# <u>ክብር ለአርበኞቻችንና ለተጋድሏቸው!</u>

አርበኞቻችንንና ተጋድሏቸውን እናከብራለን ስንል ምን ማለታችን ነው? እውን እነሱ የተሠውለትን፣ የተጋደሉለትን፣ ዋጋ የከፈሉለትን ዓላማና ተልእኮ ዋጋ ሰጥተን ነው ወይ በዓሉን እያከበርን ያለነው? ብለን ስንጠይቅ ከሕዝቡ በኩል እንዲያ ሊሆን እንደሚችል መገመት ቢቻልም ከወቅቱ አገዛዝ በኩል ግን ፈጽሞ እንዳልሆነ በግልጽ ማየት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም አርበኞቹ የተሠውለት ዓላማና አገዛዙ የፈጸመውና እያስፈጸመው ያለው ዓላማ ተቃርኖ ያላቸው ናቸውና፡፡

ርበኞች ሉዓላዊነቷ ለተከበረላት ለታፈረች ለተከበረች ኢትዮጵያ፣ ማንነቷ ታሪኳ መለያዋ ወዘተረፈዋ ለተከበረላት ለተጠበቀላት ኢትዮጵያ፣ አንድነቷ የተጠበቀላት ኢትዮጵያ ወዘተረፈ. መሥዋዕትነትን ከፈሉ፡፡ ወያኔ ኢትዮጵያን ከመበታተን ጀምሮ ማንነቷን ታሪኳን መለያዋን ወዘተረፈዋን ለማጥፋት ለማዋረድ ለመሻር ለመቅበር መሥዋዕትነትን ከፈለ ሉዓላዊነቷ የተደፈረ የተናቀች የተዋረደች ሀገር ፈጠረ፡፡

እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስ እናትና አባት አርበኞች የአድዋ ድልን፣ የየካቲት 12 የሠማዕታ መታሰቢያ በዓልን፣ የሚያዚያ 27 የድል በዓልን በየአደባባዮቹ ሲያከብሩ ለተጋድሏቸው ትርጉም የሚሰጡ የሚይዟቸው ሁለት ዋና ዋና ነገሮች ነበሯቸው፡፡ አንገቷ ያልተቆረጠችና የተጋደሉላትን የኢትዮጵያን ካርታ (ምሥለ ምድር) እና ባለ ረጅም ታሪኩን የሀገራችን ነገሥታት መለያ ምልክት የሆነው ዘውድ የደፋ አንበሳ ያለበትን ባለግርማ ሞገሱን ሰንደቅ ካልሆነም ንጹሑን የኢትዮጵያን ሰንደቅ፡፡

እሽ ከተባለና ከተፈቀደለት ወያኔ ሲነካው የማይረክስ ነገር የለምና እነኝሁን አርበኞች ነካካቸው መሰለኝ ከአራት አምስት ዓመታት ወዲህ ግን እነኝህ እናትና አባት አርበኞቻችን በበዓላቶቹ ቀናት ይዘውት የሚወጡት አንገቷ የተቆረጠች እነሱ ያላስረከቧትን የኢትዮጵያን ካርታ (ምሥለ ምድር) እና ወያኔ ከኢጋንንት አምላኪዎች ተውሶ ምልክቱ ያደረገው ባለ አምስት ጎን ኮከብ የተለጠፈበትን ጨርቅ ይዘው ይወጣሉ፡፡

ይሄም ብቻ አይደለም እነኙሁ አርበኛ ተብየዎች በብዙኃን መገናኛዎች ቃለ መጠይቅ ሲደረግላቸውም ከአንድ የወያኔ ካድሬ ባልተናነሰ የወያኔን ፖለቲካ (እምነተ አሥተዳደር) እንደጉድ እያነበነቡ የወያኔ ባንዳ በመሆን በሀገራቸውና በሕዝባቸው ላይ ክህደት በመፈጸም እራሳቸውን አዋርደው እኛንም አሳፍረውናል እጅግ አሳዝነውናል፡፡

በአሁኑ ሰዓት የአርበኞች ማኅበርን በመምራት ያሉት በሙሉ ማለት ይቻላል ሀገርንና ሕዝብን የከዱ የወያኔ ካድሬዎች ናቸው፡፡ ወያኔ በሌሎች ማኅበራት ላይ እንደሚያደርገው ሁሉ ሻጥር በመፈጸም ሀቀኞቹን በማስወገድ ቦታውን የራሱ ባንዶች እንዲቆጣጠሩት አድርጓል፡፡ ጊዜያዊ ቢሆንም በዚህ ወራዳ ተግባሩ እጅግ እናዝናለን፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com

http://www.ethiopanorama.com